

# አፈ-ወርቅ - እጅ-ወርቅ!



(ለሜይትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ መታሰቢያ)





















ከዚያች ትንሽ አምባ  ከአፍሪቃዊት መንደር፣
ከታሪካዊቷ  የሸዋ  አንኮበር፣
ማለዳ ተነስቶ  - ጥቁር አፈር ፈጭቶ፣
ቅጠሉን አቅልሞ  - የተፈጥሮን ጸጋ ጥበቡን ተጠቅሞ፣
የጀመረው ዳዴ. . .  - ወፏ ስትቆም ባንዴ. . .፣
ጥበቡ ጎምርቶ  - ሸራ አስዘርግቶ፣
ባለም ዙሪያ ናኘ  - ማዕረግ አገኘ፤
ልክ እንደ ምኒልክ  አገሩን አኮራ፣
ከጽንፍ-አጽናፍ ድንበር  በዝና አስጠራ!

በዕውቀት ረቂቅ ጥልቀት  በጥበብ ስምረቱ፣
በሃሳብ ምጥቀት ባሕር  በታሪክ እውነቱ፣
በቡሩሹ ሹል ጫፍ  ሸራ እየዳሰሰ፣
የኢትዮጵያን ዝና  ላለም አዳረሰ።
ክቡር ነው ተግባሩ!  ለእማማ አገሩ!

ኢትዮጵያዊነቱን  - የሰው ዘር ዕትብቱን፣
ያትንኩኝ ባይነት ንፁህ ነጻነቱን፣
ተፈጥሮ ግኝቱን  - አለላ ውበቱን፣
ሰብአዊነቱን  -  ሰንሰለት ሕብረቱን፣
የትውልዱን ተስፋ  ልምለሜ ራዕይ፣
ውስጠ-ምናብ ጥልቁን  አሻግሮ አሚያሳይ፣
የክህነት ውርስ-ቅርስ  አብነት ትውልዱ፣
አፈ-ወርቅ፤ እጅ-ወርቅ  “ወልደ-ነጎድጓዱ”!
ይሄ ክቡር ጀግና መኩሪያ ነው ላገሩ፣
ሲከበር ይኖራል፤  በማያልፈው ግብሩ!!

አፈ-ወርቅ፣ እጅ-ወርቅ  -  ለምለሙ ተክላችን፣
ጀግንነት ክብራችን  -  ባህል ታሪካችን፣
ትውፊት ዕሴታችን  -  ጌጥ ክብር ሃብታችን፣
የኛነት ምስላችን  -   ሁልጊዜም አብሯችን፣
በየሳሎናችን!

የዕደ-ጥበብ አድማስ - የኢትዮጵያችን ተስፋ፣
የጠቢባን ቁንጮ  - አበ-ስዕል አንጋፋ!
ሊቀ-ጥበብ ሎሬት  ሜይትር አርቲስት ያለም፣
ይኖራል ውስጣችን፤  በናት አገራችን. . .
ክቡር ሕያው ስሙ ገኖ ለዘልዓለም!

ጌታቸው አበራ
ሚያዝያ 2004 ዓ/ም
(አፕሪል 2012)

---

*ይህች ግጥም የተጻፈችው ሰኔ 1999 ዓ/ም (ጁላይ 2007) የተከበሩ  ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽን የዓመቱ የክብር እንግዳ ሆነው ተጋብዘው በነበረበት ወቅት  ሲሆን፣ በወቅቱ አጋጣሚውን በመጠቀም፣  በዳላስ የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ  ለሎሬት አፈወርቅ ባዘጋጀው የእራት ግብዣ ላይ በክቡርነታቸው ፊት በንባብ ተሰምታለች።

EthioLion.Com